# በቤ/ጉ/ክ/መ/መ/አስ/ቢሮ የኢንቨ/ማስፋ/ እና ማበረታታት ዳይሬክቶሬት

# የቀጣይ 10 ዓመታት (ምእተ ዓመት) ከ 2013 - 2022 ዓ.ም እስትራተጅክ ዕቅድ

ግንቦት/2012 ዓ.ም

አሶሳ፤

# ማዉጫ

**አርዕስት** **ገጽ**


1 ? ???...3

2 የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች - የሁለተኛዉ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም ...4

2.1 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት /የግቦች አፈፃፀም/ ...4

2.1.1 የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ...4

2.1.2 ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ...5

2.1.3 የኢንቨስትመንት ልማትን ማስፋፋት ...5

2.1.4 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ሥርዓትን ማሻሻል...6

2.1.5 ተቋማዊ አሠራርን ማሳደግ ...6

2.2 ያጋጠሙ ቁልፍ ችግሮች ...6

2.3 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች...7

3 ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ...7

4 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች...8

4.1 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች እና ዉጤቶች ...8

4.2 የትኩረት መስኮች መግለጫ ...8

4.2.1 የትኩረት መስክ አንድ - የላቀ ኢንቨስትመንት ልማት...8

4.2.2 የትኩረት መስክ ሁለት - ስትራቴጂያዊ አጋርነት ...8

4.3 ስታራቴጂያዊ ዕይታዎች...8

5 ስትራቴጂያዊ ግቦች እና መግለጫቸዉ ...9

5.1 የትኩረት መስክ አንድ - ስራቴጅያዊ ግቦች እና መግለጫቸዉ...9

5.2 የትኩረት መስክ ሁለት - ስራቴጅክ ግቦችና መግለጫቸዉ ...11

6 የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ...13

6.1 በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አካበቢ መሬት አስተዳደርና ኢንቨስትመንት ቢሮ የኢንቨ/ዘርፍ የ10 ዓመት ዉጤት ተኮር ዕቅድ (2013-2022) ...15

7 በዕቅድ አፈፃፀም የሚጠበቁ ዕድሎች /መልካም አጋጣሚዎች/ እና ስጋቶች ...19

7.1 ዕድሎች /መልካም አጋጣሚዎች/ ........ 19

7.2 ስጋቶች ........ 19

8 የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ........ 20

9 የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 21

## 1 መግቢያ

የሀገሪቷን የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠንና የህዝቦቿን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ኢንቨስትመንትን በማስፋፋትና በማበረታታት የሀገር ዉስጥ የማምረት አቅምን በማጠናከር የካፒታል ፍሰትን ለማሳደግና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በመፍጠር የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሁለተኛዉን የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከግብ ለማድረስ የኢንቨስትመንት ዘርፉ የማይተካ ሚና ስላለዉ መንግስት የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎችን በማዉጣት ሲተገብር መቆየቱ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሰረት የክልሉ መንግስት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ የሚያጋጥሙ የመልካም አስተዳደርና የተለያዩ ተግዳረቶችን እልባት እንዲያገኙ በማድረግ እንዲሁም ለልማቱ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠሩ ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች እየጨመረ መጥቷል፡፡

የክልሉ ኢንቨስትመንት ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል የሀብት አማራጮችን በመለየትና በተለያዩ ሚዲያዎች በማስተዋወቅ በርካታ ልማታዊ ባለሃብቶች በልማቱ እየተሳተፉ የሚገኙ ሲሆን ወደ ስራ የገቡትንም የአፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ በማበረታታትና ልማቱ ቀጣይነት እንዲኖረዉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ህብረተሰቡ የልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆንና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለዉጥ እንዲመጣ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የተቋሙን ራዕይ፣ ተልዕኮ፤ እሴቶች እና የትኩረት አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ በሁለተኛዉ የዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ወቅት የታዩ ምርጥ ተሞክሮዎች ተጠናክረዉ እንዲቀጥሉ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በማስተካከል የ10 ዓመታት ዕቅድ ማቀድ ያስፈለገ ሲሆን ዕቅዱን በተቀመጠዉ የአፈፃፀም ስልት እና የማስፈፀሚያ መረሃ ግብር መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ የሥራ ዕቅድ ዝርዝር በማካተት ተዘጋጅቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ኢንቨስትመንት ዘርፉ ሀገሪቱን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የማይተካ ሚና እንዳለዉ በመገንዘብ የ10 ዓመት ዕቅዱ ሲዘጋጅ አስፈላጊውን ውጤት ለማስመዝገብ እንዲያግዝ ከክልሉ ከፍተኛ አመራር አካላት ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው እርከን የሚገኘው ሙያተኛ/ሠራተኛ እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው አጋር አካላትና ባለሃብቶች በጋራ በመሆን ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትንና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያበረክተዉን ሚና ለማሳደግ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

ብቁና ተወዳዳሪ የባለሃብቶችን ፍሰት በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ክልሉ ለመሳብና ዉጤታማ ለማድረግ ለቀጣዩ ምእተ ዓመት አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር ተግባራትን ከነመለኪያዎቹ ማስቀመጡ ለዕቅዱ አፈፃፀም ወሳኝነት ያለው ጉዳይ ስለሆነ በአግባቡ ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሠረት በምእተ ዓመቱ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት፣ የሁለተኛዉ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፣ መወሰድ የሚገባቸዉ የመፍትሄ አቅጣጫዎች/እርምጃዎችና የሚጠበቁ ምቹ አጋጣሚዎችን በማካተት በዉጤት ተኮር ሥርዓት መሠረት የተቃኘ የቀጣይ 10 ዓመታት (ምእተ ዓመት) ዕቅድ እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡

## 2 **የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች** - የሁለተኛዉ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም

### 2.1 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት /የግቦች አፈፃፀም/

የክልሉን የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጮችን በመለየት፣ ማጥናትና በማስተዋወቅ፤ ሀብቱ ጥቅም ላይ እንዲዉል ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር፤ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን አፈፀፀም በመከታተልና የሚከሰቱ ችግሮችን በመፍታት በክልሉ የግሉን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት በሁለተኛዉ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወቅት በዳይሬክተሩ የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርበዋል፡-

#### 2.1.1 የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ

የኢንቨስትመንት መስፋፋት ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ በመገንዘብ የሥራ ክፍሉ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን፤ በዚሁ መሠረትም የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን በማሻሻል የተገልጋይ እርካታን 74% ለማድረስ ታቅዶ 69.66% የተከናወነ ሲሆን የተገልጋዩን እርካታ ከወትሮዉ በተሻለ መንገድ ለማሳደግ በዘርፉ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ከነዚህም መካከል የአስተያየት መስጫ ሳጥኖች እንዲሰሩ ተደርጓል፣ የዜጎች ቻርተር መግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቷል፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን ቀልጣፋ ማድረግ፣ በአዲሱ ምደባ መሠረት የሰራተኞች የደረትና የጠረንጴዛ ባጅ በአዲስ እንዲዘጋጅ ተደረጓል፣ አቅጣጫ ቋሚ እና መረጃ ሰጪ ታፔላዎችን ማዘጋጀት፣ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮች ኢንቨስት እንዲያደረጉ የሀብት አማራጭ ጥናት ማድረግ ተችሏል፡፡

2.1.2 ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

የኢንቨስትመንት ሥራዎች በባህሪያቸው የህብረተሰቡን ተሳትፎ የሚጠይቁ ከመሆናቸው የተነሳ ህብረተሰቡ የልማቱ ሁለንተናዊ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በዚህ መሠረት በዘርፉ ብዙ የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ሊያደረጉ ለሚችሉ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት እና ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ተሠርተዋል፡፡ ፕሮጀክቶችም ቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም የማምረት/አገልግሎት የመስጠት አቅማቸው እየጎለበተ ሲሄድም ዘርፉ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የራሱን አዎንታዊ አስተዋጸኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

በዚሁ መሠረት ባለሀብቶችን በአዲስ መልክ ወደ ኢንቨስትመንት ልማት በማሳተፍ ለ69,040 ቋሚ እና 181,580 ዜጎች ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር በታቀደው መሠረት በበጀት ዓመቱ ለ 40,117 ቋሚ እና 133,777 ዜጎች ደግሞ ጊዜያዊ የስራ እድል ይፈጥራሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ለ46,515 ቋሚ እና ለ176,900 ጊዜያዊ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር የታቀደ ሲሆን፤ በመስክ በተደረገው የ690 ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ሥራ መሠረት 41,527 ቋሚ እና 141,946 ጊዜያዊ በድምሩ ለ 183,473 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በበጀት ዓመቱ 690 ለሚሆኑ ፕሮጅክቶች የክትትልና ድጋፍ ሥራ ተሠርቷል፡፡

2.1.3 የኢንቨስትመንት ልማትን ማስፋፋት

የኢንቨስትመንት ልማትን በማስፋፋት የክልሉን ማኅበረሰብ ሁለተናዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እና ዘርፉ ለኢኮኖሚው ዕድገት የበኩሉን አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዲያበረክት ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡ ከነኝህም ተግባራት ዉስጥ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጮችን በማጥናትና በማስተዋወቅ በሁለተኛዉ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለ 2,390 ፕሮጀክቶች አዲስ የአንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ 2,292 ፕሮጀክቶች አዲስ የአንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት ኢንቨስት የተደረገ የካፒታል መጠንን ከነበረበት 6.112 ቢሊዮን በሁለተኛዉ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወደ 7.935 ለማድረስ ታቅዶ 6.913 ቢሊዮን ማድረስ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ለኢንቨስትመት አገልግሎት የሚዉል መሬት መረጃን ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመለየትና ለፕሮሞሽን ለማመቻቸት 355,199 ሄ/ር መሬት መረጃ በማዘጋጀት ለልማታዊ ባለሀብቶች ለማስተዋወቅ ታቅዶ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመኑ ለ 857,800

ካ/ሜ ለከተማ ኢንቨስትመት እና ለግብርና ኢንቨስትመት የሚሆን 351,709 ሄ/ር በድምሩ 362,100 ሄ/ር መሬት መረጃ ለማሰባሰብ/ለማጠናቀር ተችሏል፡፡

2.1.4 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ሥርዓትን ማሻሻል

በገጠርም ሆነ በከተማ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚደረገውን የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ ማስፋፋት እንደሚገባ ይታመናል፡፡ በዚህ አግባብ ወደ ትግበራ ለገቡ 810 ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለ656 ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ሁሉም ባለሀብቶች በገቡት ውል መሠረት የልማት ስራቸውን እያካሄዱ መሆናቸውን ወቅቱን ጠብቆ ከማረጋገጥ አንፃር ሲታይ ያለው የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ውስንነት ይስተዋልበታል፡፡ ለዚህም ከበጀትና ሎጅስቲክ ዕጥረት እንዲሁም በክልላችን ብሎም በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስተዋለ ያለዉ የፀጥታ ችግር በዋነኛነት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

2.1.5 ተቋማዊ አሠራርን ማሳደግ

የአሠራር ሥርዓቱን በማሻሻልና በማሳደግ ለአገልግሎት ፈላጊ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሻለ አገልግሎት መስጠት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ መሆኑ ይታመናል፡፡ በዚሁ መሠረት የነበረውን ተቋማዊ አሠራር በመፈተሽ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ 2 የአሰራር ሰነዶችን የተዘጋጀ ሲሆን 2 ሰነድ ስራ ላይ ለማዋል ተችሏል፡፡ ይህም በኢንቨስትመንት ክትትልና ድጋፍ ዘርፉ መረጃ አወሳሰድ የሚስተዋሉን የአሰራር ውስንነቶችን ለመቅረፍ አንድ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ ሰነድ እና ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት ለዜጎች ለመስጠት የዜጎች ቻርተር የተዘጋጁበት ሂደት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከአሰራር ግልጽኝነት ጋር ተያይዞ የመንግስት እና የዜጎች ሀብት እንዳይደበላለቅ እና የአሰራር ግልጽኝነት በተሟላ ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግ ለ25 የዳይሬክተሩ ሰራተኞች በሙስናና በብልሹ አሰራር ዙሪያ ትምህርት በመስጠት ሁሉም ሰራተኞች ሀብትና ንብረታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተደረጓል፡፡

2.2 ያጋጠሙ ቁልፍ ችግሮች

- ✓ የዘርፉ አደረጃጀት በዳይሬክቶሬት ደረጃ ብቻ ተንጠልጥሎ መቅረቱ እና የተጠናው የBPR ሰነድ በሚመለከተው አካል አለመጽደቅ ጋር ተያይዞ ስራዎችን በተፈለገዉ ደረጃ ያለማከናወን፣

- ✓ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጮችን ለማጥናት፣ የፕሮሞሽን ስራዎችን በሰፊው ለማከናወንም ሆነ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ ስራዎችን ለማከናወን የተሽከርካሪ እና የበጀት ዉስንነት፤
- ✓ የኢንቨስትመንቱ እንቅስቃሴ የፀጥታ ችግር ምክንያት መገታቱ፤
- ✓ ለከተማም ሆነ ለግብርና ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች በወቅቱ እና በተገቢዉ ሁኔታ የተለየና የተዘጋጀ መሬት በሚመለከታቸው አካልት ተዘጋጅቶ አለመቅረብ፤
- ✓ በወረዳ ደረጃ ኢንቨስትመንት ነክ ጉዳዮችን በባለቤትነት ተቀብሎ የሚሰራ አካል ያለመኖር፤

## 2.3 የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ☞ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ባለቤት ከመስጠት አንፃር በወረዳ ደረጃ ከአካ/መ/አስ/ኢንቨ/ጽ/ቤት አንድ ባለሙያ ተወክሎ ከመደበኛ ሥራዉ ጎን ለጎን ደርቦ እንዲሠራ ተደርጓል፤
- ☞ በተፈቀደልን በጀት አግባብ ከአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመግባባት የዳሰሳ ጥናት ሰነድ የተጠናቀቀ ሲሆን የተመረጡ 16 ፕሮጀክት ፕሮፋይ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ የፕሮሞሽን ሥራዉም በተቻለዉ አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ተከናዉኗል፡፡
- ☞ ባለሀብቶች ፕሮጀክቶቻቸዉን ተረጋግተዉ እንዲተገብሩ የክትትልና ድጋፍ ሥራ ተሠርቷል፡፡
- ☞ የኢንቨስትመንት መረጃዎችን በተመለከተ በተቻለዉ መጠን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በአካል በመወያየት መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ተሠርቷል፡፡

# 3 ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች

በክልሉ ቀጣይነት ያለዉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት እንዲኖር በማድረግ የኅብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፡፡

# 4 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች

## *4.1 ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች እና ዉጤቶች*

- **የትኩረት መስክ አንድ** - የላቀ ኢንቨስትመንት ልማት

  **ዉጤት** ፡ ያደገ ኢንቨስትመንት ፍሰት

- **የትኩረት መስክ ሁለት** - ስትራቴጂያዊ አጋርነት

  **ዉጤት** ፡ የጎለበተ ቅንጅታዊ አሠራር ግንኙነት

## *4.2 የትኩረት መስኮች መግለጫ*

### 4.2.1 የትኩረት መስክ አንድ - የላቀ ኢንቨስትመንት ልማት

- የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጭ ጥናት በማድረግ ተጠናከረ የፕሮሞሽን ሥራ በመሥራት ባለሃብቶች በኢንቨስትመንት መስክ እንዲሰማሩ ማድረግ፡፡
- ልማታዊ ባለሀብቶች ለሚያካሂዱት ኢንቨስትመንት ስራ አፈፃፀም የሚረዳ ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ እንዲፈጠር ማድረግ፤
- ልማታዊ ባለሀብቶች የሚያስፈልጓቸውን የኢንቨስትመንት ካፒታል እንዲያገኙ የሚያስችል የብድር አቅርቦት ማመቻቸት፤
- የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ድጋፍ መስጠት፣
- ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት መስኩ በብዛት እንዲሰማሩ በማድረግ ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማፋጠን፣
- ወደ ማምረት/አገልግሎት መስጠት የሚሸጋገሩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችንና በዳግም ኢንቨስትመንት የሚሰማሩ ባለሀብቶችን ቁጥር ማሳደግ፣

### 4.2.2 የትኩረት መስክ ሁለት - ስትራቴጂያዊ አጋርነት

- የዳይሬክቶሬቱን ሥራዎች ለማከናወን የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን በማጠናከር አፈፃፀምን ከፍ ማድረግ
- የልማታዊ ባለሃብቶች እርካታን ለማሻሻልና ተግዳረቶችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ የዉይይት መድረክ መፍጠር
- የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ስርዓት ለመዘርጋት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤
- የዳበረ አጋርነት በመፍጠር ወጥነት ያለዉ ችግር አፈታት ስርዓት መዘርጋት፤

## *4.3 ስታራቴጂያዊ ዕይታዎች*

☞ **የተገልጋይ ዕይታ፡-** ይህ ዕይታ የተመረጠበት ምክንያት ለዳይሬክተሩ ከተሰጠዉ ተግባርና ኃላፊነት አንጻር ተገልጋዩን በማገልገል ረገድ የዜጎችን ዕርካታ ለማሳደግና በሂደቱም የስራ

እድል ለመፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ነዉ፡፡ የዳይሬክተሩ ቁልፍ ተገልጋዮች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ዙሪያ የተሰማሩ ልማታዊ ባለሃብቶች ሲሆኑ ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ተገልጋዮች ናቸዉ፡፡

☞ **በጀት/ፋይናንስ ዕይታ፡-** ከመንግስት የሚመደብ በጀትን በአግባቡ ተጠቅሞ በአንስተኛ ወጪ ዉጤታማ አገልግሎት ለመስጠትና ከዳይሬክተሩ የሚገኘዉን ገቢ ለማሳደግ የሚመዘንበት ዕይታ ነዉ፡፡

☞ **የዉስጥ አሠራር ዕይታ ፡-** የዳይሬክተሩ የአሠራር ሥርዓት፣ የትኩረት መስኮችንና ዉጤት ለማሳካት እንዲሁም የተገልጋዮችንና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ለማርካት ያመች ዘንድ የሥራ አፈጻጸምና አመራርን ፣የስራ ግንኙነትና የአሠራር ስልቶችን በማቀናጀት ለተሻለ ዉጤት ለመንቀሳቀስ የሚያስችል የዕይታ መስክ ነዉ፡፡

☞ ***መማማርና ዕድገት፡-*** ይህ ዕይታ ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት እይታዎች ወደ ቁሳዊ/Tangible ዉጤት ለመለወጥ የሚያስችል አዕምሯዊ/ Intangible የሆኑ የተቋማዊ ሀብቶች የሚካተቱበት የእይታ መስክ ነዉ፡፡ በዚህ የዕይታ ሥር በዋናነት ሶስት ጉዳዮች የሚታዩ ሲሆን እነርሱም፡-የሰዉ ሃብት ፣ተቋማዊ የአሠራር ስርዓቶችና ባህል፣ አንፎርሜሽን ናቸዉ፡፡ እነዚህም ዘርዘር ተደርገዉ ሲታዩ የሠራተኞችን አመለካከት፣ ዕዉቀት፣ ክህሎት፣ ዕርካታ፣ የሰዉ ኃይል አጠቃቀምና አያያዝ፣ የአመራር ብቃት፣ የቡድን ሥራ፣ ተቋማዊ እሴትና የአሠራር ባህል፣መዋቅር፣ የህግ ማዕቀፎች የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለመለካት የምንጠቀምበት የዕይታ መስክ ነዉ፡፡

# 5 ስትራቴጂያዊ ግቦች እና መግለጫቸዉ

## *5.1 የትኩረት መስክ አንድ - ስራቴጅያዊ ግቦች እና መግለጫቸዉ*

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| ተገልጋይ | የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ | • ልማታዊ ባለሀብቱን ተሣታፊ በማድረግ ተጠቃሚነታቸዉን ማረጋገጥ፣<br>• ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታ እንዲፈጠር የማድረግ፣<br>• ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ባለሀብቶች እንዲያገኙ በመንግሥት የማስወሰን፣ | • የረኩ ተገልጋዮች |

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| | ተጠቃሚነትን ማሳደግ | • ለዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ኢንቨስትመንት በሚካሄድባቸው አከባቢዎች የሚገኘውን ህብረተሰብ ማሳተፍ | • የተፈጠረ ሥራ ዕድል |
| በጀት/ፋይናንስ | የበጀት አጠቃቀምን ማሻሻል | • በመንግሥት የሚመደብ የፐሮግራም በጀትን በታቀደው መሠረት በሥራ ላይ በማዋል ስትራቴጂያዊ ግቦችን ማሳካት፣ | • የተሻሻለ የበጀት አጠቃቀም |
| | ገቢን ማሳደግ | • የኢንቨስትመት ፍቃድ በመስጠት፣ ማደስ፣ ትክ እና ለውጥ በማድረግ ገቢን ማሳደግ፣ | • ያደገ ገቢ |
| የውስጥ አሠራር | የኢንቨስትመንት ልማትን ማስፋፋት | • ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚሆኑ የሀብት አማራጮን በማጥናት ለልማታዊ ባለሃብቱ ማስተዋወቅ<br>• በኢንቨስትመንት ዙሪያ የመጡ ለዉጦችንና ከዚሁ ጋር የሚስተዋሉ ተግዳረቶችን በማጥናት የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ<br>• ከሚመለከተዉ አካል ተዘጋጅቶ የቀረበ መሬት ለልማታዊ ባለሃብት ማስተዋወቅ<br>• ያሉትን የኢንቨስትመንት ዕድሎች እና የሚሰጡ ማበረታቻዎችን ለባለሀብቶች በስፋት ማስተዋወቅ እና የተጠናከረ ፕሮሞሽን በማከናወን ኢንቨስትመንትን መሳብ፤<br>• የኢንቨስትመንት ፈቃድ በጥራትና በፍጥነት የመስጠት፣ | • ያደገ የኢንቨስትመንት ፍሰት |
| | ክትትልና ድጋፍ ማሻሻል | • ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት እና በድህረ ኢንቨስትመንት ደረጃ የሚፈልጓቸውን መረጃዎች የመስጠት፣<br>• ለባለሀብቱ የተሰጡ የተለያዩ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው አላማ ስለመዋላቸው የመከታተል፣<br>• ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ቦታዎች ልማት ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ፣<br>• የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በዕቅዳቸው መሠረት መተግበራቸውን የመከታተል፣ | • የጎለበተ የድጋፍና ክትትል ስርዓት |

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| መማማርና ዕድገት | የአመራርና ሰራተኛ አቅምን ማሳደግ | • ተቋሙን ለመምራትና የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዘገብ በአግባቡ የሚያቅድ፣ የሚከታተል፣ የሚገመግምና በግብረ መልስ የሚጠቀም አመራርና ሰራተኛ ማበራከት፣<br>• ልማታዊ ባለሃብት በብቃት ለመደገፍ ተነሳሽነታቸው ከፍ ያለና አመለካከታቸው የተስተካከለ አመራሮችንና ሰራተኞችን ማፍራት፣<br>• የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት በተቋሙ እንዲከስምና ልማታዊ አስተሳሰብ እንዲጎለብት የሚያስችሉ ሥራዎችን በሰፊው ማከናወን፣<br>• የለውጥ ሠራዊት የሚያፈራና አስተባብሮ የሚያሠራ አመራርና ሰራተኛ ማበራከት፣<br>• የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መረጃዎች የመያዝ፣<br>• የባለሀብቶችን መረጃ በዘርፍ ለይቶ ማደራጀት፣<br>• ጥራት ያለዉ የኢንቨስትመንት መረጃዎች አቅርቦትና ተደራሽነት ሥርዓትን የማጠናከር፣ | • አቅማቸዉ የጎለበተ አመራሮችና ሰራተኞች |
| | የሥራ ከባቢን ማሻሻል | • አመራሩና ሰራተኛዉ ሥራውን በብቃትና በጥራት ለማከናወን የሚያግዘውን የተሟላ ሎጂስቲክስ ማቅረብ፣<br>• የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃን ማረጋገጥ፣<br>• ብቃትና መልካም ስነምግባር ያላቸው ባለሙያዎችን መሳብና ማቆየት የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር፣ | • የተሸሻለ የስራ አካባቢ |
| | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት ማሻሻል | • ብሮድ ባንድ ኢንተርኔት፣ ጂፒኤስ፣ እስካነር፣ ቪዲኦ ካሜራ፣ የመረጃ ኔትወርኪንግ እና ሌሎች አቅርቦቶችን ማሳደግ፤ | • ያደገ ቴክኖሎጂ አቅርቦት |
| | ተቋማዊ አሰርርን ማሻሻል | • የተቋሙን ውስጣዊ አሠራር ፣መመሪያ፣ማንዋሎችን ማዘጋጀትና ያሉትንም ወቅታዊ ማድረግ፣ | • የተሻሻለ የአሰራር ሥርዓት |

## 5.2 የትኩረት መስክ ሁለት - ስራቴጅክ ግቦችና መግለጫቸዉ

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|

| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| ተገልጋይ | የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ | • ለባለሃብቶች ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ እንዲፈጠር ማድረግ፤<br>• የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በወቅቱ ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩ ድጋፍ የማድረግ፣<br>• የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ለልማታዊ ባለሀብቶች እንዲያገኙ የማድረግ፣ | • የረኩ ተገልጋዮች |
| | ተጠቃሚነት ማሳደግ | • ለዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣<br>• የኢንቨስትመንትን በማስፋፋት በመሰረተ ልማት ዕድገት፣ በከተሞች መስፋፋት፣ በገበያ ዕድል ማደግ፣ በአካባቢ ደህንነትና እንክብካቤ፣ በቴክኖሎጂና በሥራ አመራር ዕውቀት ሽግግር የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የማሳደግ፣ | • የተፈጠረ ሥራ ዕድል |
| በጀት/ፋይናንስ | የበጀት አጠቃቀምን ማሻሻል | • በቅንጅት የሚከናወኑ ስራዎች ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መፈጸም ፣ | • የተሻሻለ የበጀት አጠቃቀም |
| የውስጥ አሠራር | ቅንጅታዊ አሠራርን ማጎልበት | • ለባለሀብቶች አሣታፊ የምክክር መድረክ በመፍጠር በህግ ማዕቀፎችና ኢንቨስትመንት ነክ ጉዳዮች ላይ መወያየት፣<br>• ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ የማቀድ፣ የመፈጸም፣ የመከታተልና የመገምገም ሥርዓት መዘርጋትና ማስቀጠል፣<br>• ችግሮችን በጋራ ተወያይቶ መፍትሄ መስጠት፣ | • የጎለበተ ቅንጅታዊ አሰራር |

| ዕይታ | የግቡ ስያሜ | የግቦች መግለጫና የሚጠበቅ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| | | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
| መማማርና ዕድገት | የመረጃ አያያዝ፣ አጠቃቀምና ልዉዉጥ ሥርዓትን ማሳደግ | • ተቋሙን ለመምራትና የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዘገብ በአግባቡ የሚያቅድ፣ የሚከታተል፣ የሚገመግምና በግብረ መልስ የሚጠቀም አመራርና ሰራተኛ ማበራከት፣<br>• ልማታዊ ባለሃብት በብቃት ለመደገፍ ተነሳሽነታቸው ከፍ ያለና አመለካከታቸው የተስተካከለ አመራሮችንና ሰራተኞችን ማፍራት፣<br>• የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት በተቋሙ እንዲከስምና ልማታዊ አስተሳሰብ እንዲጎለብት የሚያስችሉ ሥራዎችን በሰፊው ማከናወን፣<br>• የለውጥ ሠራዊት የሚያፈራና አስተባብሮ የሚያሠራ አመራርና ሰራተኛ ማበራከት፣<br>• ጥራት ያለዉ የኢንቨስትመንት መረጃዎች አቅርቦትና ተደራሽነት ሥርዓትን የማጠናከር፣ | • የጎለበተ የመረጃ ስርዓት |
| | የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሻሻል | • የአመራርና የባለሙያ አቅም በማሻሻል በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ<br>• በቴክኖሎጂ የታገዘ የአሰራር ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ | • ያደገ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም |

# 6 የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች

ደንበኛ ተኮር የመልካም አስተዳደር ሥራዎችንና የለዉጥ መሣሪያዎችን ወደ ተግባር በመለወጥ፤ በየዘርፉ ያለውን የኢንቨስትመንት ሥራ እንቅስቃሴ መረጃ በየጊዜው በማጠናከር እና ለሚመለከተው አካል በማስተላለፍ፣ አዋጪና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸዉ ፕሮጀክቶችን በማጥናት፣ ለባለሃብቶች

በማስተዋወቅና መንግስት ቅድሚያ ለሚሰጣቸዉ የኢንቨስትመንት መስኮች አስፈላጊዉን እገዛ በማድረግ፣ የኘሮጀክቶችን አፈፃፀም በመገምገም፤ ለባለሃብቶች የተሰጡ ማበረታቻዎች ለተፈለገዉ ዓላማ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን የፕሮጀክቶች **አፈፃፀም የመስክ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ማረጋገጥ፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት** የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት፤ የዘርፉን ባለሙያዎች የአጭርና ረዥም ጊዜ ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ አቅማቸዉን በማጎልበት ለደንበኞች ቀልጣፋና ጥራት ያለዉ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ከኅብረተሰቡ እንዲሁም ከባለሃብቱ ጋር በኢንቨስትመንት ዙሪያ  ዉይይት በማድረግ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን በመለየት መፍትሄ እንዲያገኙ ማስቻልና የጋራ ግንዛቤ እንዲፈጠር ማድረግ፤

## *6.1 በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አካበቢ መሬት አስተዳደርና ኢንቨስትመንት ቢሮ የኢንቨ/ዘርፍ የ10 ዓመት ዉጤት ተኮር ዕቅድ (2013-2022)*

| ተ/ቁ | አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ | የ10 ዓመት ኢላማ | የሚደረስበት ትንበያ በየበጀት ዓመቱ | | | | | | | | | | 2013-2022 ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| | **ግብ.1 የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.1.1፦ የአገልግሎት ፈላጊዎችን እረካታ ደረጃ ለማወቅ የዳሳሳ ጥናት ማድረግና ማሻሻል | በመቶኛ | 69.6 % | **95%** | 72.14 % | 74.68% | 77.22 % | 79.76% | 82.3% | 84.84% | 87.38% | 89.92% | 92.46% | 95% | |
| | ግ/ተ/ተ.1.2፦ በዜጎች ቻርተር ስታንዳርድ መሠረት አገልግሎት መስጠት | በመቶኛ | 71% | **100%** | 73.9% | 76.8% | 79.7% | 82.6% | 85.5% | 88.4% | 91.3% | 94.2% | 97.1% | 100% | |
| | **ግብ.2 የሃብት አጠቃቀምን ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.2.1፦የበጀት አጠቃቀምን ማሻሻል | በመቶኛ | 85% | **100%** | 86.5% | 88% | 89.5% | 91% | 92.5% | 94% | 95.5% | 97% | 98.5% | 100% | |
| | ግ/ተ/ተ.2.2፦ ከኢንቨስትመንት አገልግሎት ክፍያዎች ገቢ መሰብሰብ | በብር | 1,375 ,200 | **2,062,80 0.00** | 1,443,0 00 | 1,511,40 0 | 1,579, 800 | 1,648,80 0 | 1,717,80 0 | 1,786,80 0 | 1,855,80 0 | 1,924,80 0 | 1,993,80 0 | 2,062,80 0 | |
| | **ግብ.3 ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.3.1፦ በየደረጃዉ የምክክር መድረክ በመፍጠር በኢንቨስትመንት ህግ ማዕቀፎች እና ኢንቨስትመንት ነክ ጉዳዮች ዙርያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረግ | ተሣታፊ በቁጥር | 2,207 | **7,207** | 2,707 | 3,207 | 3,707 | 4,207 | 4,707 | 5,207 | 5,707 | 6,207 | 6,707 | 7,207 | |
| | ግ/ተ/ተ.3.2፦ የኢንቨስትመንት ፎረም ማዘጋጀት | በጊዜ | 3 | **10** | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | ግ/ተ/ተ.3.3፦ በአዋጅ ቁጥር 79/2001 መሠረት ከሚመለከታቸዉ ኣካላት ጋር የቦርድ አጀንዳ በመቅረጽ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ቦርድ ማቅረብ | በጊዜ | 24 | **60** | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 | 6 | |
| | ግ/ተ/ተ.3.4፦ በኢንቨስትመንት ዙርያ የሚስተዋሉ ችግሮችን በጋራ መለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ መዘርጋት | በመቶኛ | 91% | **100%** | 91.9% | 92.8% | 93.7% | 94.6% | 95.5% | 96.4% | 97.3% | 98.2% | 99.1% | 100% | |
| | **ግብ.4 የኢንቨስትመንት ልማት ማስፋፋት** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.4.1፦ አዲስ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጭ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | በሰነድ | 2 | **10** | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |

| ተ/ቁ | አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ | የ10 ዓመት ኢላማ | የሚደረስበት ትንበያ በየበጀት ዓመቱ | | | | | | | | | | 2013-2022 ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.2፦ በዳሰሳ ጥናት ከተለዩ የሀብት አመራጮች ውስጥ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡና አዋጭ የፕሮጀክት ሃሳቦችን መለየት | በቁጥር | 116 | **176** | 122 | 128 | 134 | 140 | 146 | 152 | 158 | 164 | 170 | 176 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.3፦ ለተለዩ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጭ የፕሮጀክት ሃሳቦች ጥናት በማካሄድ የፕሮጀክት ፕሮፋይል ማዘጋጀት | ፕሮፋይል በቁጥር | 100 | **176** | 116 | 122 | 129 | 136 | 143 | 150 | 157 | 164 | 170 | 176 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.4፦ ከዚህ ቀደም የተጠኑና የተመረጡ የሀብት አማራጭ ፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ወቅታዊ ማድረግ | ፕሮፋይል በቁጥር | - | **30** | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.5፦ ትግበራ ላይ ባሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የኢንቨስትመንት ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ ማዘጋጀት | ሰነድ | - | **5** | 1 | | 1 | | 1 | | 1 | | 1 | | |
| | ግ/ተ/ተ.4.6፦ ለግብርና ኢንቨ/አገልግሎት የተለየዉንና የተዘጋጀዉን መሬት መረጃ በመረከብ ለማስተዋወቅ በሚመች መልኩ ማዘጋጀት | በሄ/ር | 362,100 | **384,300** | 364,320 | 366,540 | 368,760 | 370,980 | 373,200 | 375,420 | 377,640 | 379,860 | 382,080 | 384,300 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.7፦ ለከተማ ኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚዉል መሬት ከሚመለከታቸዉ አካላት በመረከብ ለፕሮሞሽን ምቹ ማድረግ | ካ/ሜ | 1,126,405 | **2,500,000** | 1,263,764.5 | 1,401,124 | 1,538,483.5 | 1,675,843 | 1,813,202.5 | 1,950,562 | 2,087,921.5 | 2,225,281 | 2,362,640.5 | 2,500,000 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.8፦ የክልሉልን የኢንቨ/ት ሀብት አማራጮች በክልሉ ቴቪ፣ በኢብኮ፣ በፋና እና ዋልታ ቴቪ በማስተዋወቅ ባለሃብቶችን መሳብ | በጊዜ | 25 | **75** | 30 | 35 | 40 | 45 | 50 | 55 | 60 | 65 | 70 | 75 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.9፦ በኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት እና ባዛር፣ በኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ቀን፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስተመንት ሳምንት እና በአድስ ቻምበር ላይ በመገኘት የክልሉን ሀብት አማራጮች ማስተዋወቅ | በጊዜ | 16 | **56** | 20 | 24 | 28 | **32** | 36 | 40 | 44 | 48 | 52 | 56 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.10፦ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውንና አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ለሚድያ በመጋበዝ ተሞክሮዎቻቸዉን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ማድረግ | በቁጥር | 6 | **246** | 30 | 54 | 78 | 102 | 126 | 150 | 174 | 198 | 222 | 246 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.11፦ በክልሉ የኢንቨ/ት ሀብት አማራጮችን በብሮሸር እና በባነር ማሳተም | በጊዜ | 3 | **8** | 4 | | 5 | | 6 | | 7 | | 8 | | |
| | ግ/ተ/ተ.4.12፦ መስፈርቶችን አሟልተዉ ለሚቀርቡ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት | በቁጥር | 2,292 | **3,438** | 2,405 | 2,519 | 2,633 | 2,748 | 2,863 | 2,978 | 3,093 | 3,208 | 3,323 | 3,438 | |
| | ግ/ተ/ተ.4.13፦ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማደስ፣ ትክ መስጠትና ለውጥ ማድረግ | በቁጥር | 350 | **1,050** | 420.00 | 490.00 | 560.00 | 630.00 | 700.00 | 770.00 | 840.00 | 910.00 | 980.00 | 1,050.00 | |

| ተ/ቁ | አመልካቾች | | መለኪያ | መነሻ | የ10 ዓመት ኢላማ | የሚደረስበት ትንበያ በየበጀት ዓመቱ | | | | | | | | | | 2013-2022 ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| | **ግብ.5 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.5.1፡- በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | | በቁጥር | 594 | **1,653** | 719 | 791 | 870 | 957 | 1,052 | 1,158 | 1,273 | 1,401 | 1,541 | 1,653 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.2፡- ለግብርና ኢንቨስትመንት የተፈቀዱ ማበረታቻዎች ለታለመላቸዉ ዓላማ መዋላቸዉን ቁጥጥር ማድረግ | | በቁጥር | 212 | **550** | 233 | 257 | 282 | 310 | 341 | 376 | 413 | 454 | 500 | 550 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.3፡- የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመከታተል ኢንቨስት የተደረገ ካፒታል ማረጋገጥ | | በቢልየን ብር | 5.67 | **14.71** | 6.24 | 6.86 | 7.55 | 8.30 | 9.13 | 10.04 | 11.05 | 12.15 | 13.37 | 14.71 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.4፡- በከተማ ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | | በቁጥር | 202 | **817** | 232 | 267 | 307 | 353 | 406 | 467 | 537 | 618 | 711 | 817 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.5፡- ለከተማ ኢንቨስትመንት የተፈቀዱ ማበረታቻዎች ለታለመላቸዉ ዓላማ መዋላቸዉን ቁጥጥር ማድረግ | | በቁጥር | 56 | **227** | 64 | 74 | 85 | 98 | 113 | 130 | 149 | 171 | 197 | 227 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.6፡- የከተማ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመከታተል ኢንቨስት የተደረገ ካፒታል ማረጋገጥ | | በቢልየን ብር | 1.89 | **7.65** | 2.17 | 2.50 | 2.87 | 3.31 | 3.80 | 4.37 | 5.03 | 5.78 | 6.65 | 7.65 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.7፡- ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለፕሮጀክቶች ያፈጻጸም ደረጃ መስጠት | | በቁጥር | 580 | **945** | 609 | 639 | 671 | 705 | 740 | 777 | 816 | 857 | 900 | 945 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.8፡- የአፈጻጸም ክፍተት ያለባቸው ፕሮጀክቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ | | በቁጥር | 248 | **302** | 253 | 258 | 263 | 268 | 274 | 279 | 285 | 291 | 296 | 302 | |
| | ግ/ተ/ተ.5.9፡- ወደ ሥራ ለገቡ ፕሮጀክቶች የቀረጥ ነጻ መብትና የግብር እፎይታ እንዲያገኙ መፍቀድ | | በመቶኛ | 91% | **100.00** | 91.9% | 92.80% | 93.70 % | 94.60% | 95.50% | 96.40% | 97.30% | 98.20% | 99.10% | 100.00% | |
| | ግ/ተ/ተ.5.10፡ በስራ ላይ ላሉ ልማታዊ ባለሃቶች የብድር አገልግሎትና ሌሎች ድጋፎች እንዲያገኙ ድጋፍ ማደረግ | | በመቶኛ | 91% | **100.00** | 91.9% | 92.80% | 93.70 % | 94.60% | 95.50% | 96.40% | 97.30% | 98.20% | 99.10% | 100.00% | |
| | ግ/ተ/ተ.5.11፡- በተክኖሎጅ ሽግግር ዙሪያ ምርጥ ተሞክሮ ያላቸዉ ፕሮጀክቶችን በመለየት የማስፋት ሥራ መሥራት | | በቁጥር | - | **52** | 25 | 28 | 31 | 34 | 37 | 40 | 43 | 46 | 49 | 52 | |
| | **ግብ.6 ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ** | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.6.1፡- የሀብት አማራጮችን በመለየትና በማስተዋወቅ ለዜጎች ሊፈጠር የሚችል የስራ ዕድልን ማሳደግ | ቋሚ | በቁጥር | 40,117 | **120,347** | 48,140 | 56,163 | 64,186 | 72,209 | 80,232 | 88,255 | 96,278 | 104,301 | 112,324 | 120,347 | |
| | | ጊዜዊ | በቁጥር | 133,777 | **401,527** | 160,552 | 187,327 | 214,102 | 240,877 | 267,652 | 294,427 | 321,202 | 347,977 | 374,752 | 401,527 | |
| | ግ/ተ/ተ.6.2፡- የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች እና ሞደል አ/አደሮች በኢንቨስትመንት መስክ እንዲሰማሩ ማበረታታት እና መደገፍ | | በቁጥር | 168 | **668** | 218 | 268 | 318 | 368 | 418 | 468 | 518 | 568 | 618 | 668 | |
| | ግ/ተ/ተ.6.3፡-በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የተፈጠረ የስራ ዕድል | ቋሚ | በቁጥር | 41,52 | **83,057** | 45,680 | 49,833 | 53,986 | 58,139 | 62,292 | 66,445 | 70,598 | 74,751 | 78,904 | 83,057 | |
| | | ጊዜዊ | በቁጥር | 141,946 | **283,896** | 156,141 | 170,336 | 184,531 | 198,726 | 212,921 | 227,116 | 241,311 | 255,506 | 269,701 | 283,896 | |
| | **ግብ.7 የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ዉጤታማነትን ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | | | | |

| ተ/ቁ | አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ | የ10 ዓመት ኢላማ | የሚደረስበት ትንበያ በየበጀት ዓመቱ | | | | | | | | | | 2013-2022 ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| | ግ/ተ/ተ.7.1፡- ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች የኢንቨስትመንት ተሳታፊነታቸዉን ማጎልበት | በቁጥር | 56 | 196 | 70 | 84 | 98 | 112 | 126 | 140 | 154 | 168 | 182 | 196 | |
| | ግ/ተ/ተ.7.2፡- ሴቶችን የኢንቨስትመንት ተሳታፊነታቸዉን ማጎልበት | በቁጥር | 16 | 56 | 20 | 24 | 28 | 32 | 36 | 40 | 44 | 48 | 52 | 56 | |
| | ግ/ተ/ተ.7.3፡- ወጣቶች የኢንቨስትመንት ተሳታፊነታቸዉን ማጎልበት | በቁጥር | 40 | 140 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 | 110 | 120 | 130 | 140 | |
| | **ግብ.8 የአመራርና የሠራተኞችን ብቃት ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.8.1፡- በዘርፉ ፍላጎትን ያማከለ የአቅም ማጎልበቻ የዳሰሳ ጥናት ማድረግ | | - | 10 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | ግ/ተ/ተ 8.2፡- በኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ፣ ፍታኅዊና ውጤታማ ለማድረግ ለባለሙያዎች የረጅምና የአጭር ገዜ የአቅም ግምባታ ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 5 | 20 | 7 | 9 | 11 | 13 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | |
| | ግ.ተ.ተ 8.3፡- ተጨባጭ ለዉጥ ማምጣት የሚያስችሉ የአሠራር ማሻሻያዎች ላይ ከፌደራል እና የተሻለ ተሞክሮ ካላቸዉ የክልል ኢንቨ/ተቋማት ልምድ መቅሰም፤ | በጊዜ | 10 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | **ግብ.9. የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.9.1፡- የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስረዓትን ማሳደግ | በመቶኛ | 93 | 100 | 93.7 | 94.4 | 95.1 | 95.8 | 96.5 | 97.2 | 97.9 | 98.6 | 99.3 | 100 | |
| | ግ/ተ/ተ 9.2፡- ቴክኖሎጂን ለአመራርና ሰራተኛዉ ተደራሽ ማድረግ | በቁጥር | 11 | 15 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | | | | | | |
| | **ግብ.10 አዋጅ፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችና ማንዋሎችን ማዘጋጀትና ማሻሻል** | | | | | | | | | | | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.10.1፡- በዳሰሳ ጥናት ዉጤቶች፣ በየጊዜዉ በሚወጡ ክልላዊ ብሎም ሀገራዊ የኢንቨ/ህግ ማዕቀፎች እና በተቀሰሙ ተሞክሮዎች አግባብ የአፈፃፀም መመሪያዎችንና ማኑዋሎችን ማሻሻል | በሰነድ | 2 | 7 | 3 | | 5 | | 6 | | 7 | | | | |
| | ግ/ተ/ተ.10.2፡- የክትትልና ድጋፍ ማኑዋል ወቅታዊ ማድረግ | በሰነድ | 1 | 3 | | 1 | | 1 | | 1 | | | | | |

## 7 በዕቅድ አፈፃፀም የሚጠበቁ ዕድሎች /መልካም አጋጣሚዎች/ እና ስጋቶች

### 7.1 ዕድሎች /መልካም አጋጣሚዎች/

- ኅብረተሰቡ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ያለዉ ግንዛቤ እየጨመረ መሄዱ፤
- ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚዉሉ የሀብት አማራጮች መኖራቸዉ፤
- የክልሉ አየር ንብረት ለኢንቨስትመንት ምቹ መሆኑ፤
- ለኢንቨስትመንት መስፋፋት የሚያግዝ ቴክኖሎጂ አቅርቦት መረጃ ልዉዉጥ መኖር፤
- ነፃ የገበያ ሥርዓት መኖሩ፤
- የሥራ ዕድል መፈጠሩና የገቢ እድገት መታየቱ፤
- በርካታ ባለሃብቶች በዘርፉ በመሰማራታቸዉ ምርትና ምርታማነት እየጨመረ መምጣቱ፤
- የሰዉ ኃይል አቅርቦት በበቂ ሁኔታ መኖሩ፤
- የመሠረተ ልማት አገልግሎት እየተስፋፋ መሆኑ፤
- ያልተማከለ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋቱ፤
- መንግስት ለኢንቨስትመንት ልማት መስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ፤
- መንግስት ለለዉጥ ሥራዎች ትኩረት መስጠቱ እና መተግበር መጀመራቸዉ፤
- የተለያዩ የአሠራር ማዕቀፎች መኖራቸዉ፤
- የዉይይት መድረክ (ፎረም) መፈጠሩ፤

### 7.2 ስጋቶች

- የህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ የመሬት ጥበት መኖሩ፤
- የህ/ሰቡ የስራ ባህል አነስተኛ መሆኑ፤
- የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በገቡት ዉል መሰረት አለመተግበር፤
- የተፈጥሮ ሀብቱን ያለአግባብ በመጠቀም በአካባቢዉ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጠር ይችላል፤
- የገበያ ዋጋ ግሽበት መኖሩ
- ባለሀብቶች የሚሰጧቸዉን የተሸከርካሪና የብድር ማበረታቻዎች ለታለመላቸዉ ዓላማ አለማዋላቸዉ፤
- የቴክኖሎጅ ሽግግር ከሚፈለገዉ ደረጃ አለመድረሱ፤
- የለዉጥ ስራዎችን ከመተግበር አንፃር ዉስንነቶች መኖራቸዉ፤

- የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት መኖሩ፣
- የመልካም አስተዳደር ችግር መኖሩ፤
- ኢንቨስትመንትን በመሳብ በኩል ያለዉ እንቅስቃሴ የሚፈለገዉን ያህል አለመሆን፤
- ባለሃብቶች የሚፈልጓቸዉን መሬትና የተለያዩ አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ማግኘት ባለመቻላቸዉ ወደ ስራ መግባት አለመቻላቸዉ፤
- ስትራቴጅያዊ ለሆኑ ስራዎች ትኩረት አለመስጠትና በደራሽ ስራዎች መጠመድ፤
- የመረጃ ልዉዉጥ ሥርዓቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያለመደገፍና በአግባቡ ያለመጠቀም
- የሀብት አማራጭ ጥናት ያለመለየትና ሀብትን መሰረት ያደረገ የማስተዋወቅ ስራ አለመስራት፤
- ችግር ፈቺ የሆነ ክትትልና ድጋፍ አለማድረግ
- ከቅርብ ጊዜ ወድህ እየተከሰተ ያለዉ የፀጥታ ችግር ከቀጠለ ለኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዉ መሰናክል ይሆናል፤

## 8 የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት

የዘርፉ የበላይ አመራር በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላትን ማብቃት የሚያስችለውን አደረጃጀት በመፍጠር በአካልና በሪፖርት ላይ የተመሰረተ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ዘርግቶ የሚሰራ ሲሆን ከዚህ አንጻርም፣

- ☞ በተዋረድ ከባለድርሻ አካላት የሚመጣዉን ሪፖርት በየጊዜዉ በመገምገም ግብረ መልስ ይሰጥበታል፤
- ☞ የመስክ ሪፖርቶችንም ወደ ዉጤት የመቀየር ሥራ ይሠራል፡፡
- ☞ በተዘረጋዉ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መሠረት የክልል የባለሙያዎች ቡድን ወደ ዞን፤ ወረዳና ቀበሌ በአካል በመገኘት ወቅቱን ጠብቆ በቼክ ሊስት የታገዘ ድጋፍና ክትትል እንዲሰጥ ይደረጋል፤
- ☞ የበጀት ዓመቱን የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በየደረጃዉ ከሚገኙት ፈፃሚ ኃይሎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን እንዲገመገም በማድረግ ለቀጣይ ዓመታት አቅጣጫ እንዲያዝበት ይደረጋል፤
- ☞ በአጠቃላይ የለዉጥ መሣሪያዎችንና የደንበኞችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት ዕቅዳችንን ከግብ ማድረስ፡፡

- ☞ መ/ቤቱ በቻርተሩ ላይ ባለዉ አግባብ መሰረት ዜጎች ቀልጣፋና ፍትኀዊ አገልግሎት እያገኙ መሆናቸዉን የሚከታተልበት ወቅቱን የጠበቀ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥራዓት ዘርግቷል/ይዘረጋልም፡፡
- ☞ በተገልጋዮች የሚቀርቡ አስተያየቶች እና ቅሬታዎችን በመፈተሽ አስፈላጊዉን እርምትና የማስተካከያ እምጃ ይወስዳል፡፡
- ☞ የተገልጋዮች መድረክ በማዘጋጀት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በገለልተኛ ወገን የተገልጋዮችን እርካታ ለመመዘን የሚያስችል ሰርቬይ/ዳሰሳ ጥናት/ እንዲካሄድ ያደርጋል፡
- ☞ ተገልጋዮች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ደረጃ በየጊዜዉ እየገመገመ ማሻሻያዎችን ያደርጋል፡፡

# 9 የትኩረት አቅጣጫዎች

በቀጣይ 10 ዓመታት (ምእተ ዓመት) በጀት ዓመት የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች ከታች በተዘረዘሩት የትኩረት አቅጣጫዎች መሠረት በማድረግ ዕቅዱ የሚያዘጋጅ ሆኖ እንደ ዳይሬክቶሬቱ የተለዩ የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተው ቀረበዋል፡፡

- ➢ የለውጥ ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፤
- ➢ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መለየትና የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ፤
- ➢ የክልሉን ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ሀብት አማራጮች በማጥናት ኢንቨስትመንትን በክልሉ ማስፋፋትና የኢንቨስትመንት መስፋፋት በክልሉ ያመጣዉን ሁለንተናዊ ተፅዕኖ በማጥናት የአሠራር ማሻሻያዎችን ማድረግ፤
- ➢ የኢንቨስትመንት የፕሮሞሽን ሥራ መስራትና ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ በመሳብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት፤
- ➢ የተቀናጀ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ ማድረግ፤
- ➢ በፕሮጀክት ክትትል እና ግምገማ ዉጤት መሠረት የቀረጥ ነፃ፣ ብድር እና ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ በአሰራር ስርዓቱ መሰረት በስራ ላይ መዋላቸዉን በመከታተል የእርምት እርምጃ መዉሰድ፣

- ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ ለዜጎች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ሽግግር ማድረግ፣ የስራ ዕድል መፍጠር፣
- የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት እና የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም በማሻሻል የመረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት የተገልጋይን እርካታ ማሳደግ፣
- ለከተማና ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚሆን መሬት መረጃዎችን ማመቻቸት፣
- በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እየተተገበሩ ያሉ የቴክኖሎጅ ሽግግር ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የማስፋፋት ሥራ መሥራት፤
- ስራዎችና ባለሙያዎች በውጤት ተኮር ስርዓት (BSC) መሠረት እንዲመዘኑ ማድረግ፤